የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን በሚያዚያ ወር ስድስት፤ መደበኛ ስብሰባዎችን አካሂዷል፡፡ የሚያዚያ ወር ዜና መጽሔታችንም በተካሄዱት መደበኛ ስብሰባዎች የወጡ አዋጆችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን፣ የተደረጉ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን እንዲሁም ሹመቶችን አስመልክቶ በአጭሩ ለማቃኘት እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## ዓበይት ርዕሶች

- ሕግ አወጣጥ
- ክትትል ቁጥጥር
- ሹመት

መልካም ንባብ!
ሚያዚያ፤ 2018 ዓ.ም

## ሕግ አወጣጥ

## 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን መጋቢት 29/2018 ዓ.ም 14ኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል፤ በዕለቱም የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጽድቋል።





የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ ጉባኤውን ሲመሩ

ምክር ቤቱ በውሎው የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሠለሞን ላሌ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡





የተከበሩ አቶ ሠለሞን ላሌ የውሳኔ ሀሳቡን ሲያቀርቡ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው በረቂቅ አዋጁ ላይ ጥያቄዎችና አስተያየት ያነሱ ሲሆን ከግብርና ምርምር የሚገኙና ከውጭ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን የግብርና ባለሙያዎች ለአርሶ አደሮች በተግባር ማሳ ላይ እያሳዩና እያስተማሩ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው እንዲሁም ረቂቅ አዋጁ መንግሥታዊ ያልሆኑ የአገልግሎት ተዋንያን ሕጋዊነትን በጠበቀ መልኩ ተጠያቂነት የሰፈነበት እና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ መንግሥትን እና አርሶ አደሩን በመደገፍ የግብርና ልማቱን በሚገባ የሚያሳልጥ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የተከበሩ አቶ ሰለሞን ላሌ ከምክር ቤት አባላት በረቂቅ አዋጁ ላይ በተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ሲሰጡ በመንግሥት ብቻ የሚሰጠው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በቂ ባለመሆኑ ወቅቱ የሚጠይቀውን የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋ ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

እንዲሁም በዲጂታል ግብርና ኤክስቴንሽን የሚያማክሩ እና የመረጃ ቅብብሎሽ አገልግሎት የሚሰጡ የግል ባለሀብቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና የሆኑ ድርጅቶች እየታዩ በመሆኑ በግብርና ኤክስቴንሽን ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን፤ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጡ ጥራትና ፍትሃዊነት ቁጥጥር ትኩረት የሚሻ በመሆኑ አገልግሎት የሚሰጠው በተመዘገበና የብቃት ማረጋገጫ ባገኘ አገልግሎት አቅራቢ መሆን እንደሚኖርበት አዋጁ የአሰራር ሥርዓት እንዳስቀመጠ ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን መሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን ማዘመን በመንግሥት ላይ ብቻ በመውደቁ በሚጠበቀው ደረጃ እርካታ ያልተገኘበትን የተጠቃሚዎች ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት የግብርና ኤክስቴንሽን ፈንድ ለማቋቋምና ፍላጎት ለመቅረፍ ረቂቅ አዋጁ ያካተተ መሆኑን፤ እንዲሁም በግብርና ባለሙያዎች ብቻ ይሰጥ የነበረው የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሁን ላይ የምርት መጠንና ምርታማነትን ለማሳደግ በቂ ምላሽ ባለመስጠቱ ይህንን ችግር ለመፍታት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለማሻሻልና ለማዘመን ረቂቅ አዋጁ አስፈላጊ መሆኑን ሰብሳቢው አብራርተዋል፡፡





ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግ የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1411/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

በመቀጠልም ምክር ቤቱ የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የቀረበለትን ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ለዝርዝር እይታ ለዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፤





የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ አስፈላጊነት አስመልክቶ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሠ ጫፎ በሰጡት ማብራሪያ ቀደም ሲል በነበረው አዋጅ የመረጃ ነጻነትን እና መገናኛ ብዙኃንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአንድ አዋጅ መውጣታቸው የመረጃ ነጻነት ሕግ በተገቢ ሁኔታ፣ በተሟላ የአስተዳደር ስርዓት እና በአፈጻጸም ግልጽነት እንዳይቀርብ በማድረጉ እና ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር በማጣጣም የመረጃ ነጻነት አዋጅ ራሱን አስችሎ ማውጣት አሰፈላጊ በመሆኑ የቀረበ መሆኑን ገልጸዋል።

አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ ማንኛውም ሰው በመንግሥት አካል እጅ የሚገኝ መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘትና የማሰራጨት ነጻነት ይበልጥ በማረጋገጥ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን የመረጃ ነጻነት ይበልጥ ዕውን ለማድረግ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የቀረበ መሆኑንም አብራርተዋል።

የምክር ቤት አባላቱም የቀረበው ረቂቅ አዋጁ አስፈለጊ እንደሆነና የተሳሳቱ መረጃዎችን ከማረም አኳያ የአዋጁ መውጣቱ የተሻለ እንደሆነና ለዝርዝር እይታ የሚመራለት ቋሚ ኮሚቴ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲያየው ጠቁመዋል፡፡

ምክር ቤቱም የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ቁጥር10/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ ለዝርዝር ዕይታ ለዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ በውሎው የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን የዳኝነት አገልግሎት ለማዘመንና ተቋማዊ አሠራራቸውን ለመቀየር የተዘጋጀውን አዲስ ረቂቅ አዋጅ አስፈላጊነት ለምክር ቤቱ ሲያብራሩ ረቂቅ አዋጁ ለረጅም ዓመታት ሲሠራበት የቆየውንና አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታና ከፍትሕ ሥርዓት ለውጥ ጋር የማይጣጣመውን የቆየ አዋጅ ሙሉ በሙሉ የሚተካ መሆኑን ገልጸዋል።

አክለውም አፈ-ጉባኤው ረቂቁ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ እና ተያያዥ ማነቆዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን እንዲሁም ረቂቅ አዋጁ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አደረጃጀትና የዳኞች ምልመላ ሥርዓት ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ፣ የፍትሕ ሥርዓቱን ተዓማኒነት ለማሳደግ ትኩረት እንደሰጠም ገልፀዋል፡፡

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው፣ ረቂቅ አዋጁ የሚመራለት ቋሚ ኮሚቴ አዋጁ ዘመኑን የዋጀ እና የሕዝበ ሙስሊሙን ፍላጎት ያሟላ እንዲሆን ልዩ ትኩረት እንዲደረግበት አሳስበዋል።

ምክር ቤቱም የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 11/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ ለዝርዝር ዕይታ ለህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በሌላ በኩል 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ሚያዝያ 13 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 15ኛ መደበኛ ስብሰባው የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጽድቋል።



የተከበሩ ፈትሂ ማህዲ(ዶ/ር የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርቡ

ምክር ቤቱ በዕለቱ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አዋጅን ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የውጭ ግንኙነትና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ፈትሂ ማህዲ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው በረቂቅ አዋጁ ላይ ጥያቄዎችና አስተያየት ያነሱ ሲሆን በአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚሰበሰበው ክፍያ በቀጥታ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ገቢ እንዲሆን የቀረበው ሐሳብ ከመንግሥት የፋይናንስ አሠራር ጋር የሚጋጭ መሆኑን፣ ማንኛውም የመንግሥት ተቋም የሚሰበስበው ገቢ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል አልፎ በበጀት መልክ ሊመደብ ሲገባው፣ በቀጥታ ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ገቢ እንዲሆን መደረጉ አግባብ እንዳልሆነ በጥያቄ አንስተው፣ ክፍያው በቀጥታ ከአገልግሎት ተጠቃሚው ዜጋ ላይ መሆኑ የመርህ ችግር እንዳለበትና ለወደፊቱ እንደ ፖሊስ ላሉ ሌሎች የጸጥታ አካላትም ዜጎች በቀጥታ እንዲከፍሉ በር ሊከፍት ይችላል የሚል አስተያየት በረቂቅ አዋጁ ላይ አንስተዋል፡፡

የተከበሩ ምክትል ሰብሳቢ ፈትሂ ማህዲ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት በረቂቅ አዋጁ ላይ በተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ሲሰጡ ማሻሻያ የተደረገው አገሪቱ የገባችውን ዓለም አቀፍ ግዴታ ለማሟላትና የአቪዬሽን ደህንነትን ይበልጥ ለማጠናከር መሆኑን አብራርተው፣ ተቋሙ በአቪዬሽን ደህንነት ላይ ለተሰማሩ ግብረ-ኃይሎች የቴክኒክ ድጋፍ፣ ሥልጠና እና የደህንነት ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ክፍያው ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ገቢ እንዲሆን መታሰቡን ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም አሠራሩ ከመንግሥት የፋይናንስ መርህ ጋር እንደማይጋጭና ከዚህ ቀደምም በሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን በኩል በተመሳሳይ መልኩ ሲተገበር የቆየ መሆኑን ምክትል ሰብሳቢው ጠቁመዋል። ሆኖም ተቋሙ በራሱ አሰባስቦ ለሥራው ማስፈጸሚያ እንዲያውለው መፈቀዱ አሠራርን ለማቅለል እንጂ፣ መሠረታዊ የፋይናንስ ሕግን ለመጣስ እንዳልሆነ አብራርተዋል።

በዓለም አቀፍ የሲቪል አቭዬሽን ስታንዳርድና መለኪያ መሠረት የተሻለ የአቭዬሽን ሴኩዩሪቲ መገንባት የሚያስችል፤ እንዲሁም እንደ አገር ከዚህ በፊት የነበረውን መልካም ገጽታ ለማስቀጠል የሚያስችል ማሻሻያ አዋጅ ስለመሆኑም የተከበሩ ፈትሂ (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ እንደ አገር ሲያስመዘግብ የነበረውን ከፍተኛ ውጤት ለማስቀጠል ወቅቱን የዋጀ የሕግ ማዕቀፍ በማበጀት ለዓለም ማህበረሰብ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ አስተማማኝና ቀልጣፋ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት እንደሚያስፈልግና ነባሩ አዋጅ 432/1997 ከ20 ዓመታት በላይ ያለማሻሻያየቆየበመሆኑዘመኑያመጣቸውንውስብስብሕገወጥጣልቃ ገብ ድርጊቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስለመሆኑም አንስተዋል፡፡

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1412/ 2018 አድርጎ በ 2 ተቃውሞ እና በ 2 ድምፅ ተአቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል፡፡

በመቀጠልም ምክር ቤቱ የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፡፡

ምክር ቤቱ የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ ለምክር ቤቱ በንባብ አሰምተዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE









የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ የውሳኔ ሀሳብ ሲያቀርቡ

የምክር ቤቱ አባላት በበኩላቸው የአዋጁን ተፈፃሚነት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚባው አስተያየታቸውን አቅርበዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ ምላሽና ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን የፌደራል ስፖርት ልማትና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ በስፖርቱ ዘርፍ አካታች፣ አሳታፊ፣ ዘመናዊና አስተዳደራዊ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ምቹ መደላድል የሚፈጥር መሆኑ፤ በዘርፉ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የሚፈታና የስፖርት መሠረተ ልማትንና ማሰልጠኛ ተቋማትን በመገንባትና የስፖርት ግብዓት አምራቾችን የሚያበረታታ መሆኑን፤ አዋጁ ለሃገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የራሱን ድርሻ ሊያበረክት የሚችል፤ በዜጎች መካከል ማህበራዊ ትስስርን የሚያጎለብት እንዲሁም

ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር፤ ስፖርት ነክ ወንጀሎችን በመከላከል ስፖርትን ማስፋፋት የሚያስችል መሆኑን አብራርተዋል፡፡

እንዲሁም የባህልና ስፖርት ሚኒስትሯ የተከበሩ ወ/ሮ ሸዊት ሻንካ የአዋጁን አስፈላጊነት ለምክር ቤት አባላት ማብራሪያ ሲሰጡ ስፖርት የኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ እንዲሆን ዘርፉን የያዙትን ማነቆዎች በአሠራርና ሥርዓት መፍታት ያስፈልጋል ሲሉ የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት ጠቁመዋል።

አክለውም የስፖርቱ ዘርፍ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን በማድረግ በዘርፉ ለሚስተዋሉ ማነቆዎች ምላሽ የሚሰጥና አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ በማድረግ ረገድ አዋጁ ጉልህ ሚና እንዳለው ለምክር ቤቱ ገልፀዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1413/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

## ሕግ አወጣጥ

ምክር ቤቱ ሁለት የብድር ስምምነቶችን መርምሮ አጸደቀ፤
የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 20 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 17ኛ መደበኛ ሁለት የብድር ስምምነቶችን መርምሮ አጽድቋል፡፡

በዕለቱ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተፈረመውን የ80 ሚሊየን ዩሮ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ መርምሮ አጽድቋል፡፡

የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) የብድር ስምምነቱን አስፈላጊነት ለምክር

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE



የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ሲያቀርቡ

ይህ የብድር ስምምነት መንግሥት የጀመረውን የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዕቅድ ለመደገፍ የሚያግዝ የቀላል ብድር ስምምነት መሆኑንና ገንዘቡ መንግሥት እያከናወነ ያለውን ሥር ነቀል የኢኮኖሚ ለውጥ፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ እና የኢነርጂ ዘርፍ እንቅስቃሴዎችን ለማገዝ የሚውል መሆኑን የተከበሩ ምሕረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) ብድሩ በቀጥታ ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት የሚፈስ፣ ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥና የመንግሥትን የበጀት አቅም ለማጠናከር ታስቦ የቀረበ ነው ሲሉ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡ የብድር ስምምነቱ የወለድ መጠን በዓመት 1.1 በመቶ ዝቅተኛ ወለድ የሚታሰብበት፣ 0.5 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ የሚፈጸምበት እና የ5 ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ15 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ ነው ብለዋል፡፡

ምክር ቤቱ በስምምነቱ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1414/2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

በተያያዘም ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ መንግሥት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ማህበር መካከል የተፈረመውን የ110 ሚሊዮን ዩሮ የብድር ስምምነት አዋጅ መርምሮ አጽድቋል፡፡

የብድር ስምምነቱ አስፈላጊነት በቤተሰብ ደረጃ ገቢን በማሳደግ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን የመቋቋም አቅምን በማሻሻል የኑሮ ሁኔታን ማሻሻል እና ድህነትን መቀነስ መሆኑን የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) በማብራሪያቸው ቀደም ሲል በነበሩት በሁለቱ ዙሮች በአጠቃላይ 7 ሚሊዮን ለሚሆኑ በገጠሪቱ የአገራችን ክፍሎች ለሚኖሩ ዜጎች አገልግሎት በመስጠት ተጠቃሚ ማድረጉንና በቀጣይ ዙር የበለጠ ለማጠናከርና የተጠቃሚውን ቁጥር ከ13 ሚሊዮን በላይ ለማድረስ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

ብድሩ የሚተገበረው ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በሚገባ በመልሶ ማበደር የብድር ስምምነት መሰረት ባንኮችን፣ ማይክሮ ፋይናንሶችን እና የገጠር ቁጠባ እና ብድር ማህበራት ዩኒየኖችን በመጠቀም በማኑፋክቸሪንግ ፣ በአገልግሎት፣ በንግድ፣ በቱሪዝም እና በግብርና ዘርፎች ለተሰማሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ለስራ ፈጣሪዎች የሚቀርብ ነው ብለዋል፡፡

የብድር ስምምነቱ በ25 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ፣ በአውሮፓ ህብረትና ከግብርና ልማት ፈንድ የተገኘው የእርዳታ ድጋፍ የመልሶ መክፈያ ወጪን በመቀነስ ከአገራችን የብድር አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ የቀረበ መሆኑን ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል፡፡

ምክር ቤቱ በስምምነቱ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1415/2018 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

መጨረሻም ምክር ቤቱ የቁልፍ መሠረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ሪፖርትና የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርብ ለዝርዝር ዕይታ ለውጭ ግንኙነትና ሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቷል፡፡

**ምክር ቤቱ ሚያዝያ 22 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 18ኛ መደበኛ ስብሰባው የተለያዩ ረቂቅ አዋጆዎችን መርምሮ ለዝርዝር እይታ ለውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡**

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) የሁሉንም ረቂቅ አዋጆዎችን አስፈላጊነት ለምክር ቤቱ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡



የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ሲያቀርቡ

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) የሁሉንም ረቂቅ አዋጆዎችን አስፈላጊነት ለምክር ቤቱ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጆች ላይ ሰፊ ወይይት ካደረገ በኋላ ፤-

•በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥትና እና በሴራሊዮን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 13/2018፣

•በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በአንጎላ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 14/2018፣

•በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በባንግላዲሽ ሕዝባዊ ረፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ረቂቅ አዋጁ ቁጥር 15/2018፣

•በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በኢስዋቲን ንጉሠ ነገሥት መንግሥታት መካከል የተደረገውን የአየር አገልግሎት ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 16/2018፣

•በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መካከል የጋራ የባዮሎጂ ምርምር ማዕከል ለማቋቋም የተፈረመውን ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ረቂቅ አዋጅን ቁጥር 17/2018፣
በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት እና በቬትናም ሶሻሊስት ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የዲፕሎማቲክ ወይም ኦፊሻል የአገልግሎት ፓስፖርት ለያዙ ሰዎች ቪዛን ለማስቀረት የተፈረመውን ስምምነት

ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ መርምሮ ረቂቅ አዋጅን ቁጥር 18/2018 አድርጎ በሙሉ ድምፅ ለዝርዝር እይታ ለውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡

## ክትትል ቁጥጥር

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ በዕለቱ በአካሄደው 16ኛ መደበኛ ስብሰባው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን የ2018 በጀት ዓመት የ9 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያዳመጠ ሲሆን በቀረበው ሪፖርት ላይ የምክር ቤት አባላት ጥያቄዎችና አስተያየቶች አንስተዋል፡፡



ክቡር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሲያቀርቡ



የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ከምክር ቤት አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ሲሰጡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በበጀት ዓመቱ አዲስ ፕሮጀክት ሳይጨመር የቆዩ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

እንዲሁም ባለፉት ዘጠኝ ወራት አራት ነባር ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ፣ የስድስት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም የሁለት ፕሮጀክቶች የዲዛይን ክለሣ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል፡፡

ክቡር ሚኒስትሩ ከምክር ቤት አባላት የተሰጡ አስተያየቶችን እና ግብዓቶችን በመውሰድ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን በየደረጃው ቀጣይነት ያለው የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በልዩ ትኩረት በመፈጸም ቀጣይ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር እንደሚሠራ ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል፡፡

በመቀጠልም የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲሃ አህመድ እንደገለጹት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ተስፋ ሰጭ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከ20 ዓመታት በፊት ጥናት እና ዲዛይን የተሠራላቸው፣ ግንባታቸው የተጀመሩ እና ያልተጀመሩ 45 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ ማሻሻል መቻሉ፤ እንዲሁም ባለፉት ዘጠኝ ወራት የፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የዲዛይን ክለሣ ሥራ እንዲሁም ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታር ግንባታ ሥራዎች መስራት መቻሉ ገልፀዋል ፡፡

በሌላ መልኩ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅተኛ አፈጻጸም ያሳዩ እንዲሁም ጥናትና ዲዛይናቸው የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች በሁሉም አካባቢዎች በፍትሐዊነት እንዲተገበሩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራበት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ሚያዚያ 20 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 17ኛ መደበኛ ሰብሰባ የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወ/ሮ ሠላማዊት ካሳ ከምክር ቤት አባላት ለቀርቡላቸው ጥያቄዎች በቃል የሰጡትን ምላሽና ማብራሪያ አዳምጧል፡፡

ምክር ቤቱ በውሎው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶችን ከመጠበቅ እና ከማልማት አኳያ ምን እየሠራ ነው ሲል ለቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ሠላማዊት ከሣ ጥያቄዎችን አንስቷል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE



ክብርት ወ/ሮ ሠላማዊት ካሳ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሲያቀርቡ





እንዲሁም እንደ አገር ያሉ የቱሪዝም ሀብቶችን መዝግቦ ከመያዝ፣ ከመንከባከብና ከመጠገንና ካላቸው አገራዊ ፋይዳ አንጻር ጥበቃ ከማድረግ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች አንጻር የተሠሩ ስራዎች ምንድን ናቸው ሲሉ የምክር ቤቱ አባላት ጥያቄዎችን አቅርበዋል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ሠላማዊት ካሣ በማብራሪያቸው ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያስብሏት በርካታ ቅርሶች እንዳሏት ገልጸው ቱሪዝም ከ5ቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን የአገሪቱ ታሪካዊ ቅርሶች ለትውልድ እንዲተላለፉ ብሎም ከቱሪዝም የሚጠበቀውን ኢኮኖሚ እንዲያመነጩ አስፈላጊውን ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው ብለዋል፡፡

ጉዳት የደረሰባቸውን ቅርሶች ከቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመሆን የጉዳቱን መጠን በመለየት ደረጃ በደረጃ እየተጠገኑ መሆኑን የገለጹት ክብርት ሚኒስትሯ መሠረተ ልማቶችን በሟሟላት ረገድ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል፡፡

ክብርት ወ/ሮ ሠላማዊት አክለውም በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከ800 በላይ የቱሪዝም መስህቦች የተመዘገቡ መሆናቸውን ገልጸው ከ300 ያላነሱት ደግሞ በተመጣጣኝ ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልማት የሚችሉ መሆናቸውን በጥናት መለየት መቻሉን ለምክር ቤቱ ገልጸዋል።

በገበታ ለአገር፣ በገበታ ለትውልድና በገበታ ለሸገር ድንቅ የሆኑ የቱሪስት መሥህብ ሥራዎች መሠራታቸወን እና ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ ምድረ-ቀደምት መሆኗን በዓለም ለማስተዋወቅ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል ሲሉ ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

## የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ አመት የሥራ ዘመኑ ሚያዚያ 29 ቀን 2018 ዓ.ም 19ኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል፡፡






ክቡር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) የመሥሪያ ቤቱን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፓርት ሲያቀርቡ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

ክቡር ሚኒስትሩና የሥራ ባልደርቦቻቸው ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ፊቲያ አህመድ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግብረ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የሀገሪቱ የውሃ ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን፣ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ከመጠቀም አንጻር የገጠርና የከተማ ማህበረሰብ ክፍሎችን የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን አፈጻጸም ከፍ ማለቱ፣ ኤሌክትሪክ ላልደረሰባቸው አካባቢዎች የሶላር ኢነርጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መቻሉን የተከበሩ ፊቲያ አህመድ በጥንካሬ አንስተዋል፡፡

የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕሮጀክቶች፣ የአንድ አንድ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ጥናት ክለሳ እንዲሁም ድርቅ በሚከሰትባቸው አካባቢዎች እየተሠሩ ያሉ የውሃ አቅርቦት ሥራዎች አፈፃፀም ቋሚ ኮሚቴው በእጥረት የገመገመ መሆኑን ገልጸው በአፋጣኝ በዕቅድ ተይዘው መሰራት አለባቸው ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

## ዜና ሹመት

ምክር ቤቱ ሚያዝያ 15 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 16ኛ መደበኛ ስብሰባው የተጓደሉ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አመራሮችን ሹመት መርምሮ አጽድቋል፡፡

የተጓደሉ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አመራሮችን ለማሟላት የቀረቡ እጩ ኮሚሽነሮችን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሠ ጫፎ የውሳኔ ሀሳብ በንባብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል።











ምክር ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ክቡር ሚዛኔ አባተ (ዶ/ር) የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር፣ ክብርት ወ/ሮ አሸነፈች አበበ የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ዘርፍ ኮሚሽነር፣ ክቡር አቶ መሃመድ አህመድ የአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ጉዳዮች ዘርፍ ኮሚሽነር እንዲሁም ክቡር አቶ በዳሳ ለሜሳ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ኮሚሽነር አድርጎ በአንድ ድምጸ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ የውሳኔ ቁጥር 9/2018 አድርጎ አፅድቋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

ኮሚሽነሮችም በምክር ቤቱ ቀርበው ቃለ መሃላ ፈጽመዋል፡፡



## ኮሚሽነሮች በምክር ቤቱ ቀርበው ቃለ መሃላ ፈጽመዋል፡፡

ምክር ቤቱ ሚያዝያ 22 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 18ኛ መደበኛ ስብሰባው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስራ አመራር ቦርድ አባላት ሹመት መርምሮ አጽድቋል፡፡

የሹመቶችን የውሳኔ ሃሳብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ(ዶ/ር) አቅርበዋል፡፡







በዚህ መሰረት ምክር ቤቱ በቀረበው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ ሰብሳቢ እና አባላት ሹመት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ከተወያየ በኋላ

1.ወ/ሮ ብሌን ማሞ - የቦርድ ሰብሳቢ
2.ክብርት ፈዲላ ቢያ - አባል

3.አቶ ተስፋዬ ዘውዴ - አባል
4.አቶ መሐመድ ካሳ - አባል
5.አቶ አፈወርቅ በደዊ - አባል
6.ወ/ሮ አስማ ረዲ - አባል
7.አቶ ዮናስ በቀለ - አባል
8.አቶ ሀፍታይ ገ/እግዚአብሔር አባል
9.ኢሳያስ ካሳ (ዶ/ር) - አባል

የስራ አመራር ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 10/2018 በማድረግ በአንድ ድምፅ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ ሾሚል።



ተሿሚዎች በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ መሃላ ፈጽመዋል፡፡

## ለበለጠ መረጃና አስተያየት

### አድራሻ (Address)


ስልክ Tel:- 011-13-49-70
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ.ሜይል E-mail info@hopr.gov.et



በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፣ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፣